# የብፁዕ ወቅዱስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቸስኮስ መልእክት

## ለ62ኛው የዓለም የጥሪ ጸሎት ቀን

## ግንቦት 03 ቀን 2017ዓ.ም.

<u>የተስፋ ነጋድያን - የሕይወት ስጦታ</u>

ውድ እህቶች እና ወንድሞች፤

በዚህ በ62ኛው የዓለም የጥሪ ጸሎት ቀን ላይ ሕይወታችሁን ለጋስነት የታከለበት ስጦታ አድርጋችሁ በማቅራብ የተስፋ ነጋድያን እንድትሆኑ አስደሳችና የሚያበረታታ ግብዣን ላቀርብላችሁ እወዳለሁ።

ጥሪ እግዚአብሔር በልባችን የዘራው ውድ ስጦታ ነው፤ ይህም ራሳችንን ትተን የፍቅርና የአገልግሎት ጉዞ የመጀመር ጥሪ ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ጥሪ እግዚአብሔር ለዚህ ዓለምና ለእያንዳንዱ ልጆቹ፣ ለምእመናንና ለገዳማውያን ያለው የተስፋ ምልክት ነው። በአሁኑ ጊዜ ብዙ ወጣቶች የወደፊቱን ሲመለከቱ በጣም ይደነግጣሉ። ብዙውን ጊዜ ስለ ሥራ እድላቸው፣ ስለ ጥልቅ የማንነት፣ የትርጉምና የእሴቶችን ቀውስ ሲመለከቱ ግራ እየተጋቡ ሲሆን የዲጂታል ዓለም መልእክቶች ደግሞ እነዚህን ነገሮች እያባባሱ በጣም ተስፋ እንደሌላቸው ሆነው እንዲሰማቸው አድርገዋቸዋል። የድሆችና ለችግር የተጋለጡ ሰዎች ኢፍትሃዊ አያያዝ፣ የቸልተኛና የራስ ወዳድ ማኅበረሰብ ግድየለሽነት፣ እና የጦርነት ጭካኔ ወጣቶች በልባቸው ውስጥ የሚንከባከቡትን አርኪ የሕይወት ተስፋቸውን በስጋት ላይ ይጥላሉ፤ ነገር ግን የሰውን ልብ የሚያውቀው ጌታ እኛን ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ አይተወንም። እርሱ እኛ የተወደድን፣ የተጠራን እና የተስፋ ነጋድያን ሆነን የተላክን መሆናችንን እንድናውቅ ይፈልጋል።

እኛ የቤተክርስቲያኒቱ ጎልማሳ አባላት እና በተለይም ካህናት የወጣቶችን የጥሪ መንገድ እውቅና እንድንሰጥ፣ እንድንገነዘብ እና አብረን እንድንሆን ተጠርተናል። እናንተ ወጣቶች በበኩላችሁ ሕይወታችሁን የፍቅር ስጦታ ለማድረግ ፍላጎት ካለውና በሚያነቃቃችሁ መንፈስ ቅዱስ ጋር በመሆን በዚያ መንገድ እንድትሄዱ ተጠርታችኋል።

***ልዩ ጥሪያችንን ስለመቀበል***

የተወደዳችሁ ወጣቶች፣ "ወጣትነታችሁ 'ለነገ' የሚባል አይደለም። እናንተ ለእግዚአብሔር 'አሁን' ናችሁ" *(ንጽ. ክርስቶስ ሕያው ነው፣ 178)*። የሕይወት ስጦታ ለጋስ እና ታማኝ ምላሽ እንደሚሰጥ እወቁ። ለጌታ ጥሪ በደስታ ምላሽ የሰጡትን ወጣት ቅዱሳን እና ብጹዓን ለምሳሌ፡- የሊማ ቅድስት ሮዝ፣ ቅዱስ ዶሚኒክ ሳቪዮ፣ የሕፃኑ ኢየሱስ ቅድስት ቴሬዛ፣ የሐዘንተኛይቱ እመቤታችን ቅዱስ ገብርኤል፣ በቅርቡ የሚታወጁ ቅዱሳን ብጹዕ ካርሎ አኩቲስ እና ብጹዕ ፒዬር ጆርጂዮ ፍራሳቲ እና የሌሎችንም አብነት ተመልከቱ።

እነዚያ ቅዱሳን ከሙታን ከተነሳው ጌታ ጋር የነበራቸውን ወዳጅነት እንደ እውነተኛ ደስታ መንገድ በማጣጣም ጥሪያቸውን ተለማምደውታል። የኢየሱስን ቃላት ስንሰማ ልባችን በውስጣችን ይቃጠላል *(ንጽ. ሉቃ. 24:32)* እና ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር የመስጠት ፍላጎት ይሰማናል። መጀመሪያ ጌታ በተፈጥሮ እንዴት እንደወደደንና የሚወደንን ፍቅር እንድንመልስ የሚያስችለንን የአኗኗር ዘይቤ ለማግኘት የሕይወትን መንገድ እንፈልጋለን።

እያንዳንዱ ጥሪ አንዴ በልብ ጥልቀት ውስጥ በግንዛቤ ከተተከለ ራስን የማስተዋወቅ ዘዴ ሳይሆን የተስፋና የበጎ አድራጎት መገለጫ ሆኖ ለፍቅርና ለአገልግሎት መነሳሳትን ይፈጥራል። ጥሪ እና ተስፋ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ አብረው ይሄዳሉ ማለትም ለእያንዳንዱ ወንድ እና ሴት በስማቸው ተጠርተው ላሉት ሁሉ ሕይወታቸውን ለሌሎች ደስታ እንዲሰጡ ያበረታታል *(ንጽ. የወንጌል ደስታ፣ 268)*። ብዙ ወጣቶች እግዚአብሔር የሚመራቸውን መንገድ ለማወቅ ይፈልጋሉ። አንዳንዶች ብዙ ጊዜ ወደ ክህነት ወይም ለምንኩስና ሕይወት እንኳ እንዴት እንደተጠሩ ይገረማሉ። ሌሎች ደግሞ የጋብቻ እና የቤተሰብ ሕይወት ጥሪን ውበት የወል መልካም ተግባር የማከናወንና በጓደኞቻቸው እና በሚያውቋቸው ሰዎች መካከል እምነት የመመስከር ሕይወት እንደሆነ ይገነዘባሉ።

እያንዳንዱ ጥሪ መንፈሱ የሚነሳሳው በተስፋ በእግዚአብሔር ጥበቃ ላይ በመተማመን ነው። ለክርስቲያኖች ብሩህ ተስፋ ማለት በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ እየሠራ ባለው በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነት ላይ በተመሰረተ እርግጠኝነት ሲሆን ይህም የሰው ልጅ ከሚሰጠን ተስፋ በላይ ነው። ጥሪ ብስለት የሚኖረው ለወንጌል ታማኝ ለመሆን በሚደረገው የዕለት ተዕለት ጥረት ውስጥ በጸሎት፣ በማስተዋል እና በአገልግሎት አማካይነት ነው።

ውድ ወጣት ወዳጆቼ ሆይ፤ በእግዚአብሔር ላይ ያለው ተስፋ አያሳፍርም፤ ምክንያቱም በእያንዳንዱ እርምጃ ሕይወታቸውን ለእሱ አደራ ከሚሰጡ ሰዎች ጋር አብሮ ይጓዛልና፡፡ ዓለማችን ተስፋ ሰጪ የሆኑና በድፍረት ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ያደረጉ፣ ደቀ መዛሙርቱ እና ልዑካኑ በመሆናቸው የሚደሰቱ የተስፋ ነጋድያን የሆኑ ወጣቶችን ትፈልጋለች፡፡

## *የጥሪ መንገዳችንን በማስተዋል መጓዝ*

የጥሪያችን ውጤት የሚገኘውና የሚመጣው በማስተዋል ጉዞ ነው፡፡ ጉዞውም በክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥ እንደ ማኅበረሰቡ አካል ሆኖ የሚያድግ ነው እንጂ አንድ ሰው በፍፁም ብቻውን የሚያደርገው አይደለም፡፡

ውድ ወዳጆቼ ሆይ፤ ዓለም የችኮላ ውሳኔዎችን እንድትወስዱና ለልባችሁ የሚናገረውን እግዚአብሔርን በጽሞና ልባችሁን መክፈት መለማመድን በሚያግድና ወደማያቋርጥ፤ ወደሚያውክ ጩኸት ይገፋፋችኋል፡፡ ልባችሁ የሚነግራችሁን ለማዳመጥ ቆም በሉ፤ እግዚአብሔርን ስለ እናንተ ስላለው ሐሳብና ዕቅድ ለመጠየቅ ድፍረት ይኑራችሁ፡፡ በሕይወታችን ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ጥሪ እንዴት መስማት እንዳለብን አውቀን በነፃነት ምላሽ ለመስጠት ከፈለግን የጽሞና ጸሎት አስፈላጊ ነው፡፡

በማስተዋል ለሚደረግ የጽሞና ጸሎት ሕይወታችንን ስጦታ ካደረግን ሁላችንም የተስፋ ነጋድያን መሆናችንን እንድንረዳና ከሁሉም በላይ ራሳችንን ከቁሳዊና መንፈሳዊ ተድላ የተገለለ ዳርቻ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች አገልግሎት በመስጠት የጥሪ እርካታን ማግኘት እንደምንችል እንድንገነዘብ ይረዳናል፡፡ ብዙ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ራሳቸውን እንደተገለሉ፣ እንደቆሰሉ እና እንደተተዉ ሆነው እየተሰማቸው በሚጮኹት ጩኸት የደነቆሩ ብዙዎች የእግዚአብሔርን ጥሪ እየሰሙ ጆሮአቸውን ወደ እነርሱ መመለስ አልቻሉም፡፡ እያንዳንዱ ጥሪ ብርሃንና መጽናናት እጅግ በሚያስገልግበት ስፍራ ሁሉ የክርስቶስ በስፍራው መኖር ሕያው ምልክቶች የመሆን ተልዕኮአችንን ያጸናልናል፡፡ በተለየ መንገድ ምእመናን በማኅበራዊ ሕይወታቸውና በሙያዊ ቁርጠኝነት ለእግዚአብሔር መንግሥት "ጨው፣ ብርሃን እና እርሾ " እንዲሆኑ ተጠርተዋል፡፡

***<u>በጥሪ ውስጥ አብሮ መጓዝ</u>***

የሐዋርያዊ አገልግሎት አገልጋዮች እና የጥሪ ዳይሬክተሮች፣ በተለይም የመንፈሳዊ ምሪት ሰጪዎች፣ የእግዚአብሔርን የራሱን ትምህርት በሚያንፀባርቅ ተስፋ፣ በትዕግስት እና በእምነት ከወጣቶች ጋር አብሮ ለመጓዝ ዝግጁ መሆን አለባቸው:: በአክብሮት እና በአዘኔታ ሊያዳምጧቸው ይገባቸዋል:: ለራሳቸው ታማኝ በመሆን፣ በጥበብ የታገዙና አጋዥ መመሪያዎችን ማሳየትና ማሳወቅ መቻል አለባቸው:: በጉዟቸውም ውስጥ የእግዚአብሔርን የመገኘት ምልክቶች ለይተው እንዲያውቁ ሁል ጊዜ በትኩረት መከታተል አለባቸው::

በተለያየ የሰው ልጅ ሕይወት እና እንቅስቃሴ ውስጥ ጥሪን ለማበረታታትና ለማዳበር ግለሰቦች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለጌታ ድምፅ ምላሽ ለመስጠት እንዲችሉ ልባቸው ክፍት እንዲሆን ለመርዳት የተቻለውን ሁሉ ጥረት እንድታደርጉ አሳስባለሁ:: ከዚያም በትምህርት እና በሐዋርያዊ ሥራ እቅድ ውስጥ ለጥሪ በቂ ቦታ መስጠት አስፈላጊ ነው::

ቤተክርስቲያን ለጌታ በእምነትና በተስፋ “አዎን” በማለት መናገር የሚችሉ መሪዎች፣ ገዳማውያን፣ ልዑካን እና ባለትዳሮች ያስፈልጓታል:: ጥሪ በልብ ውስጥ የተከማቸ ውድ ሀብት አይደለም፤ ይልቁንም በሚያምን፣ በሚወድና ተስፋ ባለው ማኅበረሰብ ውስጥ የሚያድግና የሚጠነክር ነው:: ለእግዚአብሔር ጥሪ ማንም ብቻውን ምላሽ መስጠት አይችልም፤ ምክንያቱም ሁላችንም የወንድሞቻችንን እና የእህቶቻችንን ጸሎት እና ድጋፍ እንፈልጋለን::

የተወደዳችሁ ወጣቶች፤ ቤተክርስቲያን አዳዲስ ጥሪዎችን ስታመነጭ ህያው እና ፍሬያማ ነች:: ብዙውን ጊዜ ዓለማችን ክርስቶስን መከተል የእውነተኛ ደስታ ምንጭ መሆኑን በሕይወታቸው የሚያውጁ የተስፋ ምስክሮችን እንደአላዋቂዎች ትመለከታለች:: እንግዲህ ጌታ ለመከሩ አዳዲስ ሠራተኞችን በታላቅ ፍቅር መጥራቱን እንደሚቀጥል እርግጠኛ በመሆን ለመጠየቅ በፍጹም አንድከም:: ውድ ወጣቶች፤ በወንጌል መንገድ ላይ እንደ ተስፋ ነጋድያን መራመዳችሁን ቀጥሉ! ጌታን የመከተል ፍላጎታችሁን የቤተክርስቲያን እናትና የጥሪ እናት ለሆነችው ለማርያም ምልጃ በእምነት አቀርባለሁ:: እኔም በቡራኬዬ አብሬአችሁ አለሁ፤ ለእኔም እንድትጸልዩልኝ እጠይቃችኋለሁ::

ሮም፣ ፖሊክሊኒኮ አ. ጀሜሊ፣ እአአ 19 መጋቢት 2025

ፍራንቸስኮስ